# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

| | |
|---|---|
| ተዛማጅ ሠነዶች፡- | ABA-RB, ACA, ACA-RA, ACF, ACF-RA, ACH, ACI, ACI-RA, BLB, COC-RA, GAA, GBA-RA, GKA-RA, IGT-RA, JHF, JHF-RA |
| ኃላፊነት የሚመለከታቸው ቢሮዎች፡- | Office of the Chief Operating Officer; Office of Human Resources and Development |

## በስራ ቦታ ማስፈራራት-ዛቻ

I. **ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚያራምደውን ድርጅታዊ የመከባበር ባህል ቁርጠኝነት ማረጋገጥ

"የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACH" ተግባራዊ የማድረግ ሂደት ለመዘርጋት፣ የስራ ቦታ ጉልበተኝነት፣ ማስፈራራት በስራ ቦታ የሚደርስ ጥቃትን የመከላከል ጣልቃገብነት፣ማጤን፣ ሪፖርት ማድረግ፣ስለ ጉልበተኝነት ምርመራ እና እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች።

II. **ዳራ**

በሥራ ቦታ የሚፈጸም ዛቻ እና ማስፈራራት ተቀባይነት የሌለው እና በማንኛውም ሁኔታ የማይታለፍ፣ የማይፈቀድ መሆኑን ቦርዱ ያስገነዝባል። ማናቸውም የዛቻና የማስፈራራት ባህርይ ከመከባበር ስምምነት ባህል/Culture of Respect Compact[1]የሚፃረር እና ድርጅታዊ አቅምን ከቦርዱ ዋነኛ የእሴት አቅጣጫ የሚያስት ይሆናል። በሁሉም ግለሰቦች እና ቡድኖች መካከል ሰራተኞች የመረዳት፣ የመከባበር እና አዎንታዊ መስተጋብር ለመፍጠር አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል።

III. **ትርጉም**

A. ቅሬታ አቅራቢ ሠራተኛ ማለት፡- ከሚመለከታቸው ህጎች፣ የቦርድ ፖሊሲዎች እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመሪያዎች ወይም ደንቦች ጋር የሚጻረር ድርጊት ተፈጽሞብኛል በማለት ቅሬታ አቅራቢ አካል ነው።

B. ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ማለት ቅሬታ ያቀረበ(ች) ግለሰብ ወይም ግለሰቦች፣ እርምጃ መውሰድ ያለበት ማንኛውም ሰው ወይም ቅሬታውን ለመፍታት እርምጃ የሚወሰድበ(ባ)ት ሰው ወይም ሰዎች ማለት ነው።

C. በሥራ ቦታ ማስፈራራት ማለት ተደጋጋሚ የሆነ፣ ሆን ተብሎ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚጎዳ፣ በቃላት፣ በአካል ወይም በሌላ መንገድ በአንድ ግለሰብ ወይም በብዙ ሰራተኞች ላይ በሌላ ሰራተኛ ወይም ሰራተኞች አማካይነት የሚፈጸም በደል ማለት ነው፣ ይህ ማለት –

[1] የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የመከባበር ባህል፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር ሕብረት፣ የአገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች ዓለም አቀፍ ሕብረት ሎካል 500፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአስተዳዳሪዎች እና ርእሰ መምህራን ማህበር (ከዚህ ቀጥሎ የመከባበር ባህል ተብሎ ይጠራል) መካከል የመከባበር ባህል።

A. በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው በማንኛውም ግለሰብ ላይ በትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት የግል ባህሪ ምክንያት የሚፈፀም ፀረ መድልዎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት፣ ወይም

B. ዛቻ ወይም ማስፈራራት፣ እና በስራ ቦታ ወይም በስራ አቀጣጠር ሂደት ላይ የሚከሰት ድርጊት፣ እና

C. የግለሰብን የሥራ ቦታና ሁኔታ ምቾት ለመንሳት የሚሠነዘር ከባድ ድርጊት ነው።

ድርጊቱ የተፈጸመው MCPS ንብረት ውስጥ ቢሆን ወይም ከ MCPS ንብረት ውጪ፤ ይህ አይነት ባህርይ በአካል ወይም በማንኛውም ሌላ የመገናኛ ዘዴ፣ በኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ጭምር የሚደረግ ሊሆን ይችላል።

የሥራ ቦታ ዛቻና ማስፈራራት በሱፐርቫይዘር እና በበታች ሠራተኛ መካከል ብቻ የሚወሰን ባህርይ ሳይሆን በሥራ ባልደረቦች መካከል ወይም ከበታች ሠራተኛ በሱፐርቫይዘር ላይ የሚሰነዘር ባህርይን ጭምር ያካትታል። የሥራ ቦታ ዛቻና ማስፈራራት ምሳሌዎች፡- ማዋረድ፣ ማሳፈር፣ ማስፈራራት፣ ወይም በሥራ ላይ አሻጥር መፈጸምን ሊያካትት ይችላል። በሥራ ቦታ የሚፈጸም ጉልበተኝነት፣ ዛቻና ማስፈራራት የግለሰብን አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ደህንነት ወይም በሥራ አፈጻፀም እና የዕድገት እድሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

## IV. የተሻለ ውጤት ለማምጣት የሚከናወን ተግባር

A. ግንዛቤ እና መከላከል

1. በሥራ ቦታ ስለሚፈጸም ጉልበተኝነት፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ መስፋፋትን በተመለከተ ምክንያቶቹን እና ስለሚያስከትሏቸዉ ዉጤቶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ግንዛቤን ያሳድጋል/ይጨምራል። የመከላከል ስልቶች እና የመረጃ ስርጭት እንቅስቃሴዎች በ MCPS ስለሚደገፍ እና ስለሚጠበቅባቸው ሙያዊ ሥነምግባር እና የሥራ ባልደረባነት ምግባር በሠራተኞች መካከል ተገቢ ግንዛቤ እንዲኖር ያጠናክራል የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ-Employee Code of Conductእና የዳበረ የመከባበር ባህል-Culture of Respect Compact።

2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ቦታ ጉልበተኝነት፣ ማስፈራራትና ዛቻን ለይቶ ማወቅ፣ መከላከል፣ ጣልቃ ገብነት፣ እና እርምት የማድረግ ግንዛቤ ለመስጠት ለሠራተኞች እና ለህብረተሰብ ቁሳቁሶችን-ማቴሪያሎችን ያሠራጫል።

3. በስራ ቦታ ጉልበተኝነትን፣ ዛቻ፣ እና ማስፈራራትን የመከላከል መረጃ፣ ስርአት አቀፍ የስራ ቦታ ስነምግባር የሙያ እድገት ስልጠና ላይ የሚካተቱ ሲሆን ይኼውም፡- በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መለየት፣ መከላከል፣ ጣልቃ መግባት እና ማስተካከልን ይጨምራል። ስለ ሥራ ቦታ ጉልበተኝነት፣ ዛቻና ማስፈራራት በሚመለከት ተግባራዊ ህጎችና ፖሊሲዎች ተዘጋጅተው ይገኛሉ።

4. በሰው ሃብት ልማት ቢሮ (OHRD)፣ የስርአት ማስከበር እና የምርመራ ክፍል (DCI) አማካይነት ተጨማሪ መመሪያ ይሰጣል።

B. ሪፖርት ስለማድረግ

1. ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ በስራ ቦታ ጉልበተኝነት፣ ዛቻና ማስፈራራት እንደተፈፀመበ(ባ)ት የሚገልጽ፣ ወይም በስራ ቦታ የሚደርስበ(ባ)ትን ጉልበተኝነት ዛቻና ማስፈራራት ያስተዋለ(ች) ተመልካች፣ ክስተቱን ወዲያውኑ

ለርእሰመምህራቸው/ለተቆጣጣሪ ወይም ለሚመለከተው የስራ ቦታ ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበ(ባ)ት። ሪፖርት ማድረግን፣ ምርመራን፣ እና በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከታተልን በሚመለከት DCI እንደ አስፈላጊነቱ ለሰራተኞች እና ለተቆጣጣሪዎች መመሪያ ያዘጋጃል።

2. የአቤቱታ አቅራቢው(ዋ) ቅሬታ የተፈጠረው ከአቤቱታ አቅራቢው(ዋ) የበላይ ተቆጣጣሪ ጋር ከሆነ፣ ወይም ቅሬታ የቀረበ(ባ)በት ኃላፊ በያዘ(ች)ው ስልጣን ምክንያት በደል ያደረሰ(ች) ከሆነ፣ ወይም ቅሬታው በአከባቢ ደረጃ ካልተፈታ ሰራተኛው(ዋ) ወይም ሁኔታውን የተመለከተ ሰው ቅሬታውን MCPS ቅጽ 230-39 በመሙላት በቀጥታ DCI የሰው ሃይል ሥርዓት ማስከበር ክፍል ኃላፊ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች። የአድልዎ ቅሬታ ወይም የስራ ቦታ ጉልበተኝነት፣ ዛቻ ወይም ማስፈራራት፣ ወይም ወደ DCI በዚህ ኢሜይል DCI@mcpsmd.org መላክ ይቻላል።

3. MCPS የሰራተኞች እና አቤቱታ የቀረበባቸው ሶስተኛ ወገኖችን ቅሬታዎችና ጥያቄዎችን ጨምሮ የምርመራዎችን ምስጢራዊነት ከሚመለከታቸው ህጎች እና እንደዚህ ያሉ ቅሬታዎችን የመመርመር እና የመፍታት ሃላፊነትን ይጠብቃል።

D. አንድ ግለሰብ በቅን ልቦና በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸም ጉልበተኝነትን ሪፖርት በማድረግ ወይም ሪፖርት እንዲደረግ በመሳተፉ ወይም በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸመውን የጉልበተኝነት ክስ በማጣራት ረገድ በመተባበር ምክንያት በማንኛውም ግለሰብ ላይ ምንም አይነት አሉታዊ እርምጃ አይወሰድም።

C. ምርመራ

1. የተጠረጠረ ድርጊት የስራ ቦታ ጉልበተኝነትን የሚያካትት መሆኑ በሚወሰንበት ጊዜ በአጠቃላይ የክስተቱ ሪከርድ እና የተከሰተበት ሁኔታ ጭምር ግምት ውስጥ ይገባል።

2. ሂደቱ በሁሉም ደረጃ ማንኛውም ፍላጎት ያለው አካል በማናቸውም የመረጡት ግለሰብ አብሮ በመሆን ሊደገፍ ይችላል።[2]

3. 60 የሥራ ቀናት ውስጥ የሰራተኛ ግብረኃይል ስርአት የማስከበር ኃላፊ -

   a) ቅሬታው በዚህ ደንብ መሠረት ለመታየት የሚችል አግባብነት ያለው መሆኑን ለማወቅ ከተገመገመ በኋላ አግባብነት ካለው፥

   b) ውንጀላውን በመመርመር፣ ውሳኔ መስጠት እና ለሚመለከታቸው ወገኖች ማሳወቅ።

4. በግምገማ ወቅት የቀረበው ቅሬታ የምርመራውን መስፈርት ካላሟላ፣ በአቤቱታው ውስጥ ለተጠቀሱት ሌሎች ወገኖች ሳያሳውቅ ጉዳዩ ለቅሬታ አቅራቢው(ዋ) ይመለሳል።

---

[2] ሠራተኛው(ዋ)ን እንዲደግፍ" የመረጡት ማንኛውም ሌላ ግለሰብ" ከሰራተኞች ጋር የጋራ ድርድር የሚደረግበት ክፍል ተወካይ በመሆን ከሰራተኛ ጋር አብሮ የሚቀርብ ወይም የሚደግፍን ሰው ሊያካትት ይችላል።

5. የተራዘመውን የጊዜ ገደብ እና ምክንያቱን በአፋጣኝ ካሳወቃቸው በኋላ የሥራ ግብረ ሃይል ሥርአት አስከባሪ ባለስልጣን አስገዳጅ በሆኑ ምክንያቶች የጊዜ ገደቡን ሊያራዝም ይችላል።

D. የሥራ ቦታ የጉልበተኝነት ጥቃት ውሳኔን ይግባኝ ማለት

1. በሥራ ግብረ ሃይል ስርአት አስከባሪ ሹም የተሰጠውን ውሳኔ ደንብ/"Regulation ACA-RA"፣ መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት፣ ሰክሽን IV.B.4 ላይ የተቀመጡትን ሂደቶች በመከተል ለዋና ኦፕሬሽን ኃላፊ ይግባኝ ማለት ይቻላል።

2. በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸም የጉልበተኝነት ጥቃት ክስ MCPS Regulation GKA-RA ውስጥ ለተገለጸው አይነት አስተዳደራዊ ቅሬታ የአስተዳደራዊ ቅሬታ የማቅረብ ሂደት ተገዢ አይሆንም።

E. የማስተካከያ እርምጃ

1. የእርምት እና ደረጃን ጠብቆ የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ-Employee Code of Conduct እና በጋራ የድርድር ስምምነቶች ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደምቦችን መሰረት በማድረግ ይወሰናል።

2. ሰራተኞች በስራ ቦታ ላይ የጉልበተኝነት ድርጊቶችን ሲፈጽሙ ወይም የበቀል እርምጃ ሲወስዱ እና/ወይም ሆን ብለው የሀሰት ውንጀላ የፈጸሙ ሰራተኞች ላይ የሚያስከትለው መዘዝ የቅጣት እርምጃ ያስወስዳል። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት የጽሑፍ ተግሣጽ/ማስጠንቀቂያ፣ ሙያዊ ምክር፣ ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግን፣ ከሥራ መታገድን ወይም ከሥራ ማሰናበትን ሊያካትት ይችላል።

F. ተቀጣሪ ሰራተኛ ባልሆነ(ች) ሰው የሚፈፀም ጉልበተኝነት፣ ማስፈራራትና ዛቻ

1. ሠራተኞች ከማህበረሰብ አባላት ጋር በሙያዊ ስነምግባር እና በመተጋገዝ ራሳቸውን ማነጽ አለባቸው። ሆኖም ግን፣ ሁሉም ሠራተኞች በሥራ ቦታዎቻቸው በሚያደርጉት መስተጋብር ሁሉ ስልጡን የግንኙነት ስነምግባር እንዲኖራቸው ይጠበቃል።

2. ከማህበረሰብ አባላት በሚደረግ መስተጋብር በሥራ ቦታ ዛቻ-ማስፈራራት በሚደርስበት ጊዜ ሠራተኞች ለሱፐርቫይዘሮቻቸው እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ። ሱፐርቫይዘሮች ሠራተኞቻቸውን እንዲደግፉ እና ሠራተኞች በሥራ ቦታቸው ላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ ባልሆኑ ሰዎች አማካይነት ስለሚደርስባቸው ጉልበተኝነት፣ ዛቻ-ማስፈራራት መፍትሔ በመፈለግ መርዳት አለባቸው። ተቀጣሪ ካልሆኑ ሰራተኞች ጋር ግንኙነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ሱፐርቫይዘሮች DCI እና/ወይም የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ጥበቃ ቢሮን ማማከር ይችላሉ።

3. MCPS ንብረት ላይ ወይም ውጪ በስራ ቦታ የሚፈፀም የጉልበተኝነት ጥቃትን በሚመለከት ስለሜሪላንድ ህግ ለሰራተኞች ያሳውቃል፣ እንዲሁም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ ላልሆኑ ሰራተኞች በአካልም ሆነ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ፣ በኤሌክትሮኒክስ ይሁን በምግባር ስለሚደረግ ግንኙነት መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ መመሪያ እና ሪሶርስ ይሰጣል።

4. በሜሪላንድ ህግ ላይ የሚገኙ ድንጋጌዎች፣ MCPS ደንብ ABA-RB፣ የትምህርት ቤት ጎብኝዎች እና MCPS ደንብ COC-RA፣ MCPS ንብረት ላይ ያለአግባብ ህግን መተላለፍ ወይም ሆን ተብሎ ሁከት መፍጠር፣አስፈላጊ ከሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ ያልሆኑ ሰራተኞች በስራ ቦታ ላይ ለሚፈፅሙት የጉልበተኝነት ጥቃት ጉዳዩን ለመፍታት የመፍትሔ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።

G. ሌሎች መፍትሄዎች

በዚህ ውስጥ ያልተካተተ ምንም ነገር በማንኛውም ሌላ የቦርድ ፖሊሲ ድንጋጌ፤ MCPS ደንብ፣ ወይም ማንኛውም የአካባቢ፣ የስቴት ወይም የፌደራል ህግ ወይም ደንብ ማንኛውንም የሙብት ጥሰት መፍትሄ የማግኘት ወይም እርምጃ አወሳሰድን የሚከለክል ወይም የሚገድብ አይሆንም። እንዲሁም በአግባቡ ተፈጻሚነት ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦች፣ እና ሒደቶችን በመጠቀም የመቆጣጠር እና የማስተዳደር ግዴታቸውን በሚወጡበት ወቅት የቦርዱን እና የሱፐርኢንተንደንቱን ሙሉ ሙብቶች፣ ስልጣን እና ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነታቸውን MCPS አይገድብም።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Culture of Respect Compact; Montgomery County Public Schools Employee Code of Conduct; Annotated Code of Maryland, Education Article, §6-901 through §6-906, and §26-101

**የደንቡ ታሪክ፡** አዲስ ደንብ ጁን 29, 2016፤ ብዙ ለውጥ ያልታከለበት ከለሳ ጁላይ 24, 2017 ተደርጓል፣ ማርች 14, 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፦ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org